# ብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው

## የቆሬው ብረት አጥር




ቆሬ ላይ መከላከያ ቦታ የተያዘበት 43ኛ ዓመት ዛሬ መስከረም 4 ቀን 2013 ታስቦ ይውላል። እኔም ቀኑን በማሰብ የተሟላ ባይሆንም የማውቀውንና በቦታው ላይ ከነበሩ የቃረምኩትን አካትቼ ላጋራችሁ ወደድኩ። ጂጂጋን ለመታደግ ከሶማሊያ ጦር ጋር ውጊያ ገጥሞ የነበረው የወገን ጦር የጠላት ኃይል ከአቅሙ በላይ ሆኖበት ከተማዋን ለመልቀቅ ተገዷል። ከዚያ ያፈገፈገው ጦር ቆሬ ላይ መከላከያ እንዲይዝ የተደረገው መስከረም 4 ቀን 1970 ዓ/ም ነበር። በሕይወት ያሉ የውጊያው ተሳታፊዎች በዛሬዋ ዕለት ወደ ኋላ መለስ ብለው ከጎናቸው የወደቁ የጦር ሜዳ ጓደኞቻቸውንና እነሱም የመድፍ ጥይት

እየወረደባቸው ለስድስት ወራት ያሳለፉትን የቀበሮ ጉድጓድ ኑሮ የሚያስቡበት ቀን ነው። ይህ ቀን መከላከያ የተያዘበት መታሰቢያ ብቻም ሳይሆን ሌላም የሚታወስበት ታሪክ አለው።

3ኛ ክ/ጦር በብ/ጀኔራል አስፋው ወ/ጊዮርጊስ አዛዥነት ጠቅላይ መምሪያውን ሐረር ላይ አድርጎ ሦስት ብርጌዶች ይዞ በ1939 ዓ/ም ተቋቋመ። ብርጌዶቹም፡- 9ኛ ብርጌድ ዋርደር፤ 10ኛ ብርጌድ ጂጂጋና 11ኛ ብርጌድ ደጋሃቡር ላይ ነበሩ። ክ/ጦሩ ሲመሠረት የአንበሳ ዓርማ መለያ ሆኖ የተሰጠው መሆኑን የሚጠቁም ተጨባጭ መረጃ ባላገኝም ጀኔራል አማን አንዶም በ1953 ዓ/ም "የኦጋዴን አንበሣ" ብለው ሰይመውታል። የክ/ጦሩ ክፍሎች ብዛትና ቦታ አያያዝ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው እየተለዋወጠ ቆይቶ ሐረር ያለው ጠቅላይ መምሪያው ወደ ዕዝ ከፍ በማለቱ ክ/ጦሩ እንደገና ከላይ በተጠቀሰው ቀን በአዲስ መልክ ዓርማውን እንደያዘ እንዲደራጅ የተደረገበት ቀን ነው።

በኢትዮጵያ የጦርነት ታሪክ በስድስት ወር ውስጥ ከፍተኛ የመድፍ ጥይት ያረፈበት የቆሬው መከላከያ ምሽግ ነው። የቆሬው ድል የተገኘው በሕይወት፤ በአካልና በአዕምሮ ዕንቁ የሆኑ የሠራዊቱ አባላት በከፈሉት ከፍተኛ መስዋዕትነት ነው። ታዲያ የነሱን ውለታ የሚያስታውስ በቦታው ላይ የቆመ መታሰቢያ የለም። ያስገኙትም ድል የሚታሰብበት ቀን የለውም። የዛሬው ትውልድ ከሐረር ጂጂጋ ሲመላለስ እንደማንኛውም ቦታ ቆሬን አልፎ ይሄዳል፤ በቦታው ላይ የቆመ ምንድነው ብሎ እንዲጠይቅ የሚያደርገው ነገር የለም። ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው ደግሞ ቆሬ ላይ የተገኘው ድል በሌላ መነጠቁ ነው።

የካራማራ የኢትዮጵያውያን ድል ተብሎ በየዓመቱ የካቲት 26 ቀን 1970 ዓ/ም ይከበራል። የኢትዮጵያ ሠራዊት ጥንት በካራማራ ተራራ ላይ ያደረገው ጦርነት የለም። በኢትዮጵያና ሶማሊያ መካከል በተደረጉ ጦርነቶች በመከላከሉም ሆነ በመልሶ ማጥቃቱ በካራማራ ተራራ ላይ የተደረገ ፍልሚያ አልነበረም። አዎ! ካራማራ ታዋቂ የሆነ ታላቅ ወታደራዊ ጠቀሜታ ያለው ስትራቴጂክ ቦታ ነው። በተለይም መከላከል ለማድረግ በጣም ቁልፍ ቦታ ነው፤ ግን አልተጠቀምንበትም። ችግሩ የተጠቃሚው ቢሆንም፤ ላላገለገለን፤ ላልተጠቀምንበት ታላቅ ታሪካዊ ስያሜ መስጠቱ አግባብነቱ አይታየኝም። የአደዋ ድል ሲባል አደዋ ላይ ጦርነት ተካሂዷል ድልም ተገኝቷል፤ ስያሜው ይገባዋል። በአንጻሩ ካራማራ ላይ ጦርነትም አልተካሄደ፤ ድልም አልተገኘ። ታዲያ በምን እሳቤ ነው የካራማራ ድል ተብሎ የሚከበረው፤ መሰየም የነበረበት በአመራር ስህተት ጂጂጋ ላይ መስዋዕት ለሆኑና ለደረሰው የጂጂጋ ውድቀት ወይም በቆሬው መከላከል የብረት አጥር ሆነው አገሪቱን ከሽንፈት ያዳኑ ጀግኖች የወደቁበትን ቦታ ነበር። በመጀመሪያ "የካራማራ ድል" ተብሎ እንዲከበር የተደረገው በፖለቲካ ውሳኔ እንጂ በታሪካዊ ዳራው አይመስለኝምና እንደገና ቢጤን እላለሁ፤ አለበለዚያ የበሬን ውለታ አህያ ወሰደው የተባለው ተረት ብጤ ይሆናል። የተዛባ ታሪክን ይዘን መቀጠል ያለብን አይመስለኝም።

የአገራችን ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው፤ በእኛ ዕድሜ እንኳ ከውጪ ወራሪ ጠላትና በውስጥ የእርስ በርስ ጦርነቶች ተካሂደዋል። ድልም ውድቀትም ገጥሟል። ለድሉም ሆነ ለውድቀቱ የጦር መሪዎች ድርሻ ከፍተኛ ነው። የጦርነት መርህ ዕውቀት አቅም ማነስና አስተባብሮ የመምራት ጉድለት ለውድቀት የዳረገ ሲሆን አቅሙ ያለው ደግሞ ለድል አብቅቷል። አቅም አጥተው ለውድቀት የዳረጉንና አቅም ኖሯቸው ለድል ያበቁንን የጦር ሜዳ መሪዎች አሁን እንኳ ባይሆን ተከታዩ ትውልድ ታሪካቸውን እየመረመረ በተገቢ ቦታቸው ላይ ያስቀምጣቸዋል ብዬ አስባለሁ።

ከዚህ አኳያ ብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው ጂጂጋ ላይ ፈረሶ በማፈግፈግ ላይ የነበረውን የወገን ጦር ቆሬ ላይ አደራጅተው በሰውና በመሣሪያ በከፍተኛ ቁጥር የሚበልጣቸው የሶማሌ አጥቂ ኃይል የሚመሩት ጦር ጥቃቱን የብረት አጥር ሆኖ እንዲመክት ለማድረግ ያካበቱት የወታደራዊ ሳይንስ ዕውቀትና የአመራር ጥበብ ለድል አብቅቷል። የቆሬን መከላከል አውደ ውጊያና የሰጡትን የአመራር ብቃት ከማንሳቴ በፊት የእሳቸውን ማንነት ላስቀድም።

ብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው የተወለዱት በሐረርጌ ወበራ አውራጃ በጨለንቆ ወረዳ ልዩ ስሙ ሐደንቃ በተባለ ቀበሌ ከአባታቸው ከአቶ ግዛው አማኑና ከእናታቸው ከወ/ሮ ዘውዲቱ ዓለምነህ ታህሣሥ 19 ቀን 1929 ነው። ብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሂርና እስከ 4ኛ ክፍል ተምረው ከዚያም አሰበተፈሪ በሚገኘው ደጃዝማች ወ/ገብርኤል አባ ሰይጣን ት/ቤት በ1945 አጠናቀዋል። ከዚያም ሐረር በሚገኘው የመድኃኒዓለም 2ኛ ደረጃ አዳሪ ትምህርት ቤት ቀጥለው በ1949 የኢትዮጵያ ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና ወስደው በከፍተኛ ማዕረግ አልፈው በ1950ዓ/ም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ይባል በነበረው የሳይንስ ፋካልቲ ገብተው የ1ኛ ዓመት ተማሪ እያሉ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር

አካዳሚ ሲከፈት በንጉሡ አማካኝነት በመጀመሪያ ከተመለመሉት ከፍተኛ ውጤት ከነበራቸው 40 ተመራጮች አንዱ ይልማ ግዛው ነበሩ፤ አካዳሚው ለመግባት ባይፈልጉም ግዴታ ነበር።

ብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው ዕጩ መኮንን ሆነው ወደ አካዳሚው ሲገቡ የፈረጠመ ደልዳላ ቁመና የነበራቸው ሲሆን በአካዳሚ ቆይታቸው ቁጥብና ዝምተኛ፤ የራሳቸው አስተሳሰብ ያላቸው፤ ትክክል ነው ብለው ያመኑበትን ከመናገርንና ከመፈጸም ወደኋላ የማይሉ የመርህ ሰው እንደነበሩ የኮርስ ባልደረቦቻቸው ይመሰክሩላቸዋል። በአካዳሚው የሚሰጡትን የአካዳሚክና የወታደራዊ ትምህርቶች በንቃት የሚከታተሉ ጎበዝ ተማሪ እንደነበሩ ከኮርሳቸው 40 ዕጩ መኮንኖች ውስጥ በጠቅላላ ውጤት 2ኛ ሆነው መመረቃቸው በቂ ምስክር ነው። ብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው በተፈጥሮ የታደሉት ብሩህ አእምሮ የነበራቸው ሲሆን በአካዳሚ ቆይታቸው በአካልና በአእምሮ የበለጠ ዳብረው ለሚጠብቃቸው ሥራ ብቁ ሆነው ተመርቀዋል።

በምድር ጦር ታንከኛ መምሪያ ተመድበው በናዝሬት የመጀመሪያ የታንክ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ በ1955 ዓ/ም ለሻምበል ደረጃ የታንክ ትምህርት ለመማር ወደ አሜሪካ አገር ፎርትኖክስ ተልከው ጥሩ ውጤት ይዘው ተመልሰዋል። ከአሜሪካ መልስ ለአካዳሚክ ትምህርት በመመረጣቸው አቋርጠውት የነበረውን ትምህርት ለመቀጠል ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ (አሁን አዲስ አበባ ይኒቨርሲቲ) ተመልሰው በ1959 በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ በማግኘት ተመርቀዋል።

ከዚያም በ4ኛ ክ/ጦር በሕግ አማካሪነት ተመድበው ሲሰሩ ቢያፍራ ከናይጀሪያ እንዳትገነጠል በነበረው የርስ በርስ ጦርነት ጊዜ በንጉሡ ነገሥቱና ጄኔራል ያኩቡ ጎዋን የናይጀሪያ መሪ መካከል በተደረገው ስምምነት በኮ/ል ነጋ (በኋላ ጀኔራል) የተመራ የኢትዮጵያ ግብረ ኃይል አባል ሆነው ወደ ናይጀሪያ ሄደው ለስምንት ወራት ያህል በታዛቢነት ሠርተዋል። ከተላኩበት ግዳጅ በተጓዳኝ ጥሩ የጦር ልምድም ቀስመው ተመልሰዋል። ከናይጀሪያ እንደተመለሱ ወደ ቀድሞ ሥራቸው ተመልሰው ሲያገለግሉ ቆይተው በ1962 ዓ/ም ወደ ተመረቁበት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ በአስተማሪነት ተዛወሩ። ብዙም ሳይቆዩ ለከፍተኛ የእግረኛ ትምህርት ተመርጠው ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አሜሪካ ፎርት ቤኒንግ ተልከው አገር የሚያኮራ ውጤት አስመዝግበው ተመልሰዋል። ከትምህርት ቤቱ ለኢትዮጵያ መንግሥት የመከላከያ ሚኒስቴር ብቃታቸውን የሚያደንቅ ደብዳቤ ተጽፏል። የአካባቢው ጋዜጦችም “ YILMA CAPTURES HONORS” ብለው ዘግበዋል።

ከአሜሪካ እንደተመለሱ የ3ኛ ክ/ጦር ረዳት የዘመቻ መኮንን ሆነው ተመደቡ፤ ብዙም ሳይቆዩ ቀደም ሲል ሲያስተምሩበት ወደነበርው አካዳሚ ተዛውረው በማስተማር ላይ ሳሉ ወደ 2ኛ ክ/ጦር የዘመቻ መኮንን ሆነው ተመደቡ፤ ከዚያም ወደ ሕብረት ዕዝ መምሪያ ተዛውረው በሥራ ላይ እንዳሉ ለታንከኛ ትምህርት ወደ ሶቪየት ሕብረት ተላኩ። በ1969 ዓ/ም አድሃሪው የሶማሊያ ጦር አገራችንን ሲወር ጀኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን አብረው ታንከኛ ሳሉ ያውቋቸው ስለነበር በእሳቸው ጥቆማ ሻለቃ ይልማ ግዛው አቋርጠው በአስቸኳይ እንዲመለሱ ታዘዙ።

ከሶቪዬት ሕብረት አዲስ አበባ በገቡ ማግሥት በሄሊኮፕተር ድሬዳዋ ከዚያም ጂጂጋ ነሐሴ 10 ቀን 1970 ገብተው የ10ኛ ሜ/ብርጌድ ዘመቻ መኮንን ሆነው ተመደቡ። የወገን ጦር የሶማሊያን ጥቃት ባልተቀናጀ መልክ ለመከላከል ሲሞክር እሳቸውም ሁኔታውን ገና ምንም ሳይረዱ ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማሪያም ነሐሴ 14 ቀን ጂጂጋ ደርሰው ስለሁኔታው የ10ኛ ሜ/ብርጌድ አዛዥ ሌ/ኮሎኔል ኃይሌ ተ/ሚካኤል ባደረጉት ገለጻ አሁን ባለው ኃይል የመሬቱ ሁኔታ ጂጂጋን ለመከላከል አመቺ ባለመሆኑ ከተማውን ለቆ ካራማራ ላይ መከላከያ ለመያዝ ያላቸውን ዕቅድ ሲያስረዱ፤ ሌ/ኮ መንግሥቱ ኃይለማሪያም ደግሞ ጂጂጋ ስትራቴጂክ ከተማ ስለሆነ ሳይለቀቅ ዙሪያውን መከላከል እንዲደረግ መመሪያ ይሰጣሉ። የብርጌዱ አዛዥ መመሪያውን ለመተግበር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ተነስተው ሌ/ኮሎኔል ይልማ ግዛው (በኋላ ብ/ጀኔራል) አዛዥነቱን እንዲረከቡ ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ አዘው በዕለቱ ተመለሱ። (ቀደም ሲል ሁለቱም በ10ኛ ብርጌድ ውስጥ አብረው ይሠሩ እንደነበር ይታወቃል። ጂጂጋን ለመከላከል አለመቻሉ የመመሪያውን ስህተትነት አሳይቷል)። እርክክቡም ሳይፈጸም የሶማሊያ ጦር ማጥቃት ሠንዝሮ ጂጂጋ የነበረው የወገን ጦር አለቃና ጭፍራው ባለየበት በተመሰቃቀለ ሁኔታ ካራማራን አልፎ ወደ ሐረር አቅጣጫ ማፈግፈግ ጀመረ። ከዚያም የሚያፈገፍገውን ጦር ቆሬ ላይ አስቁሞ መከላከያ ለማስያዝ ሐረር ላይ የነበረው 3ኛ ክ/ጦር ጠ/መምሪያ ቀዳሚ መምሪያውን ቆሬ ላይ እንዲያደርግና ክ/ጦሩ እንደ አዲስ ከየቦታው አፈግፍጎ በመጣው ጦር እንዲደራጅ የታዘዘው መስከረም 4 ቀን ሲሆን ለጊዜው በቦታው ላይ በማዕረግ ቀደምት የነበሩት ለጊዜው አዛዥነቱን የያዙት ኮ/ል እሸቱ መኮንን ከደጋሃቡር አፈግፍጎ የመጣው የ11ኛ ብርጌድ አዛዥ ነበሩ፤ ሆኖም ወዲያውኑ

የሶማሊያ ጦር ማጥቃት ከመሰንዘሩ በፊት ብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው የ3ኛ ክ/ጦር አዛዥነትን ተረከቡ። ሐረር የሚገኘውን መምሪያውንም ምሥራቅ ዕዝ ተረከበ።

"ቆሬ" የሚለው ቃል ኦሮምኛ ሲሆን ትርጉሙም "እሾህ" ማለት እንደሆነ ከቋንቋው ተናጋሪዎች ተረድቻለሁ። በእርግጥም ለሶማሊያ ጦር እሾህነቱን በተግባር ያስመሰከረ ቦታ ነው። ቆሬ በሐረር ጂጂጋ መንገድ ላይ ከሐረር 65 ኪ/ሜትር ከጂጂጋ ደግሞ 40 ኪ/ሜትር ላይ የሚገኝ ቦታ ነው። በሐረር ጂጂጋ መንገድ ላይ የሶማሊያ ሠርጎ-ገብ ደፈጣ በማድረግ እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እንዲገደቡ ለማድረግ ጥረት ሲያደርግ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ ገላጭ ሻምበል ጦር እጀባና የአካባቢ አሰሳ እንዲያደርጉ ግዳጅ ተሰጥቷቸው በየካቲት ወር አጋማሽ 1969 ዓ/ም ሲሰማሩ ጠቅላይ ሠፈራቸውን ቆሬ ላይ ነበር ያደረጉት።

ከጂጂጋ ካራማራን አልፎ ወደ ሐረር አቅጣጫ ያፈገፈገው የወገን ጦር ቆሬ ላይ እንዲቆም ሦስት ነገሮች እረድተዋል፦ 1ኛ በጦሩ ውስጥ ተሰግስገው የነበሩ ሥርዓት አልበኞች አደብ እንዲገዙ መደረጉ፤ 2ኛ የአካዳሚው ገላጭ ሻምበል ጦር በቦታው ላይ መገኘቱና 3ኛ የየመን መድፈኞች 122 ሚ/ሜ መድፍና ቢኤም 21 ይዘው ቦምባስ ትንሽ ቆየት ብሎም ቢሆን መድረሳቸው ናቸው። ጦሩ ሊረዱት በመጡ የባዕድ አገር ሰዎች ላይ ማለፍ ሞት ስለሆነበት፤ ቀጥሎ ለመጣው የጦሩ የመንፈስ ጥናትም ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። ቆሬ በመሠረቱ ወታደራዊ መሬት አይደለም። የመከላከልም ሆነ የማጥቃት ውጊያ ለማድረግ የሚመረጥ አልነበረም፤ ሆኖም ሁኔታው አስገድዶ ተይዟል። ካራማራ ላይ ሳይሆን ቆሬ ላይ መከላከያ መያዙ ለመጪው ትውልድ ወታደራዊ ተመራማሪ እንቆቅልሽ ሳይሆንበት አይቀርም።

የተከላካይ ጦር ድርጊት በራሱ ሳይሆን በግንባሩ በተሰለፈው አጥቂ የጠላት ጦር ዕንቅሳቃሴ ለይ የተመሰረተ ነው። ሐርጌሣ የሚገኘው የሶማሊያ 26ኛ ዕዝ ካራማራን ለያዘው ጦር አዛዥ፤ ጦሩ ካራማራ ላይ የሦስት ቀን ረፍትና ፌሽታ እንዲያደርግና የተላከለት አጠናካሪ ጦር እንደደረሰ ማጥቃቱን እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሲያስተላልፍ ተጠለፈ። የሶማሊያ ጦር ካራማራ ላይ የሶስት ቀናት ፈንጠዝያ ሲያደርግ ለኢትዮጵያ ጦር ግን ቆሬ ላይ መልሶ ለመቋቋምና መከላከያ ለማዘጋጀት ወርቃማ ጊዜ ነበር። የሶማሊያ ጦር እነዚህን ቀናት ባይሰጠን ኖሮ የኢትዮ- ሶማሊያ የጦርነት ታሪክ ሌላ ሥዕል ይኖረው ነበር።

በዚህ አጭር የጊዜ ገደብ ውስጥ የተከናወኑት በመጀመሪያ ክፍለ ጦሩን ማደራጀት ነበር፤ ይህ ተግባር በጀኔራል ይልማ ግዛው ብቻ የሚፈጸም ሳይሆን የሁሉንም ርብርቦሽ የሚጠይቅ በመሆኑ አዲስ የተቋቋመው ምስራቅ ዕዝ ቀዳሚ መምሪያውን ቆሬ ላይ በማድረግ ክ/ጦሩን በማደራጀት በኩል ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ይህም ለብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው ትልቅ ድጋፍ ሆኗቸዋል። በዚህም መሠረት የክ/ጦሩን መምሪያ መኮንኖች (እስታፎች)ደለደሉ።

ዘመቻ - ሻምበል አምባው ጎሣ (በኋላ ሻለቃ ሰሜን በግዳጅ ላይ የተሰዋ)

መረጃ- ሌ/ኮ ከበደ ወ/ጻዲቅ (በኋላ ብ/ጀኔራል የሰሜን ዕዝ የታደራዊ መረጃ ኃላፊ የነበሩ በመፈንቅለ መንግሥት የተገደሉ)

ድርጅት - ሌ/ኮ ከበደ መሃሪ (በኋላ ብ/ጀኔራል የሰሜን ዕዝ የድርጅት መምሪያ ኃላፊ በመፈንቅለ መንግሥት የተገደሉ)

አስተዳደር - ሌ/ኮ ባህሩ አበራ (በኋላ ኮሎኔል ጀ/ል ይልማ ግዛው ከሞቱ በኋላ ቆይቶ ለተወሰነ ጊዜ የ3ኛ ክ/ጦር አዛዥ የነበሩ)

በየሞያቸው አንቱ በተባሉ ምርጥ መኮንኖች የተደራጀ እስታፍ ነበር።

የክፍለ ጦሩ ማዘዣ ቦታ ከቦምባስ አለፍ ብሎ ከግንባር መከላከያው መስመር 3 ኪ/ሜትር ኋላ ላይ እንዲሆን ወሰኑ

ከየቦታው አፈግፍጎ የመጣውንና ለማጠናከር ከሐረር የተላከውን ጦር በ2 እግረኛ ብርጌዶች ውስጥ ተሰግስገው ክ/ጦሩ በ2 መደበኛ ብርጌድና በ1 ሕዝባዊ ሠራዊት ብርጌድ የተዋቀሩ ሲሆን ለዘመቻ ብቻ 2 ሕዝባዊ ሠራዊት ብርጌድ ተደርቧል።

ብርጌዶቹም የሚከተሉት ነበሩ፦

1 - 9ኛ እግረኛ ብርጌድ (ቀብሪደሃር በነበረው የተሰየመ) -- አዛዥ - ሻለቃ ባዩ ይርዳው ሲሆኑ በሥሩ፦ 219 ነበልባል ኃይል፤ 3ኛ ሻለቃ - (ገላዲን የነበረ) እና 18ኛ ሻለቃ - (ቀብሪደሃር የነበረ) የአካተተ ነበር።

2 - 10ኛ እግረኛ ብርጌድ (ጂጂጋ በነበረው ሜ/ብርጌድ የተሰየመ)-አዛዥ-ሌ/ኮሎኔል መርሻ አድማሱ ሲሆኑ 33ኛ ሻለቃ - (ጭናክሰን የነበረ)፤ 22ኛ ሻለቃ - (ዋርደር የነበረ)፤ 8ኛ ሻለቃ - (ቀብሪደሃር የነበረ) የያዘ ነበር።

3- 92ኛ ሚሊሽያ ብርጌድ - አዛዥ - ሌ/ኮሎኔል ከበደ አርምዴ ሲሆኑ ሻለቆቹ - 921፤ 922፤ 923 ኣና 924 ነበሩ

90ኛ ሕዝባዊ ሠራዊት ብርጌድ- አዛዥ-ሌ/ኮሎኔል ደሳለኝ አበበ (ተደራቢ) ሲሆን ሻለቆቹ፡- 901፤ 902፤ 903 እና 904 ነበሩ።

74ኛ ሚሊሽያ ብርጌድ- አዛዥ- ሌ/ኮሎኔል ይግዛው አብርሃ (ተደራቢ) ፤ ሻለቆቹ- 741፤742፤743 እና 744 ነበሩ

ቀጥሎ የተደረገው ለብርጌዶቹ የመከላከያ ቀጠና ማከፋፈል ነበር። ጀኔራል ይልማ ግዛው ለቆሬ መሬት አዲስ አልነበሩም። ዕጩ መኮንን ሆነው የሥልት ልምምድ ያደረጉበት፤ በአካዳሚው አሠልጣኝ ሆነው በየጊዜው ዕጩ መኮንኖችን ያለማመዱበት ስለሆነ መሬቱን ጠንቅቀው ማወቃቸው የቀጠና ክፍፍልና የኃይል ምደባ ለማድረግ በጣም ረድቷቸዋል።

9ኛ ብርጌድ ከሐረር ጂጂጋ መንገድ በስተግራ በኩል ሲሆን 74ኛ ሚ/ብርጌድ በዚሁ ግንባር እንዲሰለፍ ተደርጓል

10ኛ ብርጌድ ደግሞ ከመንገዱ በስተቀኝ በኩል ሲሆን

92ኛ ሕዝባዊ ሠራዊት ብርጌድ -በጉርሱም ግንባር ሲመደብ፤

90ኛ ሕዝባዊ ሠራዊት ብርጌድ የክ/ጦሩ ተጠባባቂ ሆኖ የኋላና የቀኝ ክንፍ ጥበቃ እንዲያከናውን ተደርጓል።

የመከላከያ ምሽግ አያያዝን በተመለከተ የተሰጠው መመሪያ ደግሞ፡-

ሁለቱ መደበኛ እግረኛ ብርጌዶች በተሰጣቸው ቀጠና 2ሻለቆች በግንባር የመከላከያ ቦታ እንዲያሲዙ፤ 1 ሻለቃ በሁለተኛ መከላከያ መስመር ቦታ እንዲይዝና ተጠባባቂ እንዲሆን መመሪያ ተሰጥቷል። ሁለቱ የሕዝባዊ ብርጌዶች ደግሞ 2ሻለቃ በግንባርና 2 ሻለቃ በተጠባባቂነት እንዲያሰልፉ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል።

ጠላት ድንገተኝነት እንዳያገኝ ሁሉም ብርጌዶች በየቀጠናቸው ግንባር የጠላትን ዕንቅስቃሴ እየተከታተለ የሚያሳውቅ ቃኚ ጦር በጥልቀት እንዲያሰማሩ ታዘዋል።

ቆሬ የነበሩ 2 መደፈኛ ሻለቆች ቦታ አያያዝ ደግሞ 4ኛ መድፈኛ ሻለቃ (155ሚ/ሜትር ርዕሰ-ውልብሊቢት) ከሐረር ጂጂጋ መንገድ ግራ ከ9ኛ ብርጌድ ኋላ፤ 2ኛ መድፈኛ ሻለቃ (105 ሚ/ሜትር ተጎታች) ከመንገዱ ቀኝ ከ10ኛ ብርጌዶች ቀጠና ኋላ ከመንገድ ብዙም ሳይርቁ በመረጡት ቦታ መድፋቸውን እንዲጠምዱ ተደርጓል። ከ2ኛ መድፈኛ ሻለቃ 1 ባትሪ መድፍ ጉርሱም ለ92ኛ ሕዝባዊ ብርጌድ እንዲደርብ ተደርጓል። የየመን መድፈኞችም በኋላ ሲመጡ በዚሁ አካባቢ ቦታ እንዲይዙ ተደርጓል። ከነዚህ ውጪ በወቅቱ ታንክም ሆነ ብረት ለበስ አልነበረም።

የሚቀጥለው ትልቅ ተግባር የነበረው የክ/ጦሩ አዛዥና መምሪያ መኮንኖች በብርጌዶች ቀጠና እየተዘዋወሩ የሻለቃ አመራሮች ለመታኮሻ ጥሩ ናቸው ብለው ለየሻምበሎቻቸው የመረጧቸውን ቦታዎችና የምሽግ ዝግጅቱን እያዩ እርምት መስጠትና ለዝግጅቱ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ማቅረብ ነበር፤ በተለይም ጥይትና ደረቅ ቀለብ ፤ ይህም ጉብኝት የወደቀውን የጦሩን ሞራል ለማነሳሳት ጭምር ነበር።

በሦስቱ ቀናት ውስጥ ጦሩ ቀንም ሌሊትም ያለምንም እረፍት የሠራው ምሽግ በቀላሉ የሚጣስ አልነበረም፤ ምሽጉ በዚሁ ቦታ እስከመጨረሻው የጠና አልነበረም ጊዜ ሲያመች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ማሻሻል ተደርጓል፤ ለጊዜው ግን የሚመጣውን ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል ምሽግ አዘጋጅቶ አጥቂውን የሶማሊያ ጦር መጠባበቅ ጀመረ።

የሶማሊያ ጦር የጂጂጋን ከተማ ብቻ ሳይሆን ብዙ መስዋዕትነት ያስከፍለኛል ብሎ ይገምተው የነበረውን የካራማራ ተራራን በመያዙ ከፍተኛ የሆነ ኩራት ተሰምቶት ጠላትህ ተሸንፎ ሲያፈገፍግ ሚዛኑን እንደሳተ ግብህ ድረስ እግር በእግር እየተከታተልክ አጥቃ የሚለውን ወታደራዊ መርህ በመጣስ የሚያፈገፍገውን የኢትዮጵያ ጦር መከተል አቁሞ ሦስት ቀናት በካራማራ ላይ የደስታ ጮቤ ሲረግጥ ቆየ።በዚሁ ጊዜም የጎደለውን ሰውና ድርጅት አሟልቶ ማጥቃቱን ለመቀጠል ዝግጅት ማድረግ ጀመረ።

ያለ ብዙ መስዋትነት የተገኘ ድል አስተሳሰብን ይለውጣል፤ ከእኔ ወዲያ ተዋጊ የለም፤ ከፊቴ ማን ይቆማል የሚል ዓይነት ሥነ ልቦና ይፈጥራል። በሶማሊያ ጦር መሪዎች ዘንድ በኦጋዴን ውስጥ የነበሩ የኢትዮጵያ ጦር ይዞታዎችና ካራማራን አስለቅቀን ይዘናል፤ ከአሁን በኋላ የምንፈልገው ግብ (አዋሽ) ለመድረስ የሚያግደን ኃይል የለም የሚል ዕብሪት ልባቸውን አሳብጦት ነበር። የጦራቸውም ሞራልና የመዋጋት መንፈስ ከፍተኛ ነበር። በወቅቱ የነበረው የነሱና የኢትዮጵያ ጦር የኃይል ሚዛን ሲነጻጸር የግምታቸውን ዕውነተኚነት የሚያረጋግጥ ነበር፤ ሆኖም የቁጥር የበላይነት ብቻ ለድል እንደማያበቃ ማስረጃ የሚሆኑ ብዙ ጦርነቶች አሉ ለምሳሌም የእስራኤልና የአረቦችን ጦርነት መጥቀስ ይቻላል፤ የቆሬውስ ውጊያ ሌላ ተጠቃሽ ለመሆን ይበቃ ይሆን?

በአንጻሩ የጦር ሜዳ ሽንፈት የተዋጊውን ጦር ሞራል ይሰብራል። እንደገና ለመዋጋት ያለውን ተነሳሽነት በእጅጉ ይቀንሳል፤ በቀላሉ በአጭር ጊዜ ለማገገም አስቸጋሪ ያደርገዋል። የኢትዮጵያ ጦር በአንጻሩ በአመራርና በቅንጅት ጉድለት በኦጋዴንና ጂጂጋም ላይ የደረሰበት ሽንፈት ሞራሉን ገሎ አንገቱን እንዳያስደፋው፤ ይልቁንም የደረሰበትን ሽንፈት ለመበቀል እያንዳንዱ ወታደር አእምሮ ውስጥ የበቀል ቂም እንዲቋጥር፤  እንዴት በሶማሊያ ጦር እንሸነፋለን የሚል ቁጭት እንዲያሳድር፤ በጂጂጋ ውጊያ የተሠራውን ስህተት በማሰብ ያ ዳግም እንዳይደገም እያንዳንዱ ወታደር ምን ማድረግ እንዳለበት ግንዛቤ ማስጨበጥ አዛዥ ሆነው አዲስ የተሾሙት የብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው  የመጀመሪያ ተግባር ነበር  ። ይህ ሁኔታ በሁሉም የጦሩ አባሎች ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል ብሎ ለመገመት አስቸጋሪ መስሎ ይታይ ነበር። የጂጂጋው ግርግር የፈጠራቸው ከሥነ ሥርዓት ውጪ በመሆን መከላከያ ይዘው እንደገና ለመዋጋት የማይፈልጉም ጥቂቶች አልነበሩም። ይህን የተተረማመሰ ሁኔታ ለውጦ ጦሩን በአንድ መንፈስ ከሶማሊያ ጦር የሚሰነዘረውን ማጥቃት እንዲቋቋም ማድረግ ለብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው የአመራር ብቃት የመጀመሪያው ተግዳሮት ነበር።

የመከላከል ውጊያ እንደሚታወቀው በቁጥር የበላይነት ያለውን የጠላት ጦር አግዶ ለመልሶ ማጥቃት ዝግጅት ጊዜ መግዣ እንደመሆኑ መጠን የቆሬውም መከላከል በመሃል አገር ለሚደረገው የጦርነት ዝግጅት ጊዜ መግዣ ብቻም ሳይሆን የሶማሊያ ጦር ከአዋሽ በታች ያለውን የኢትዮጵያ ግዛት ለመያዝ ያቀደውን ዕውን እንዳያደርግ ወሳኝ ፍልሚያ ነበር።የቆሬ መከላከያ ከተሰበረ በቀላሉ ሐረርና ከዚያም አዋሽ ለመድረስ የሶማሊያን ጦር ግስጋሴ ማቆም የሚችል የወገን ኃይል ለጊዜው በአካባቢው አልነበረም። ስለሆነም የቆሬ መከላከል ውጊያ በሐገራችን ላይ ትልቅ አደጋ ሊፈጥር የሚችል ሁኔታን የመመከት የሞት ሽረት ጉዳይ ነበር።

የሶማሊያ ጦር የ3 ቀን ረፍቱን ጨርሶ መስከረም 7ቀን 1970 ያጠቃል ተብሎ የወገን ጦር ዝግጁ ሆኖ ይጠባበቅ ነበር፤ ሆኖም ማጥቃቱ እስከ መስከረም 16 ቀን አልተሰነዘረም። ይህ ተጨማሪ ጊዜ የወገን ጦር ምሽጉን በደንብ እንዲያዘጋጅና አዛዦችም ከጦራቸው ጋር በደንብ እንዲተዋወቁ ዕድል ፈጥሯል።

በብ/ጀኔራል አህመድ ሰላሃን የሚመራ የሶማሊያ ጦር ከአደው አቅጣጫ መስከረም 15 ቀን 1970 ዓ/ም ወደ ፊት  ተንቀሳቅሶ ቆሬ መከላከያ ግንባር ቀርቦ አዳር አደረገ። የሶማሊያ ጦር እስካሁን ድረስ ባደረጋቸው ውጊያዎች ለድል የበቃው "የጦር ሜዳው ንጉሥ"  ተብሎ በሚጠራው መድፍ ድብደባ ነበር። ተመሳሳይ ውጤት ለማግኘት መስከረም 16 ቀን በቆሬ መከላከያ ምሽግ ላይ ጧት ጀምሮ ሙሉን ቀን እንደበረዶ የመድፍ አረር ሲያዘንብ ዋለ። ኮ/ል ይልማ ግዛውም በዚህ ድብደባ ወቅት በጦራቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ በመሆኑ ምናልባት ጦሩ ምሽጉን ለቆ ይሸሽ ይሆን የሚል ጥርጣሬና ሥጋት ነበራቸው፤ ሆኖም አንድም ተዋጊ ጦር ምሽጉን አለቀቀም። በዚህም ጠቅላላ የክ/ጦሩ አመራር  የልብልብ ተሰማው በጦሩም ላይ እምነት አደረበት።

ሌሊቱን ጠላት “የውጊያ ንግሥት” በሚባለው እግረኛ ጦር አሰልፎ አንድ ክ/ጦር በተገመተ ኃይል የሌሊት ማጥቃት ሠነዘረ። ይህ ውጊያ ለሁለቱም ተፋላሚ ኃይሎች ወሳኝ ነበር። ለሶማሊያ ጦር ግባቸውን ለመያዝ ለኢትዮጵያ ጦር ደግሞ የምሥራቅ ዕዝና የሐረር ከተማ እንዳይደፈሩ ጠላትን ማገድ ነበሩ። የጠላት እግረኛ ክ/ጦር መከላከያውን ጥሶ ለማለፍ ዋና የማጥቂያ አቅጣጫውን ከመንገዱ በስተቀኝ የመከላከያ ቦታ በያዘው 10ኛ እግረኛ ብርጌድ ግንባር በማድረግ ጦሩን በረድፍና በጥልቀት አሠልፎ በተከታታይ (wave after wave) ማጥቃቱን ቀጠለ። የወገን ጦርም በየምሽጉ ግንባር የሚመጣውን ጠላት ማየትና መግደያ መሬት እስኪገባ እየጠበቀ እንደቅጠል ማርገፍ ጀመረ፤ የክ/ጦሩ አመራር መከላከያው እንዳይሰበር በቅርብ እየተከታተለና በሰው ኃይል እያጠናከረና የቡድን መሣሪያዎች ተኩስ በዚህ ግንባር አስተባብሮ በመምራት ድርሻውን ተወጥቷል።

ጎህ ሲቀድ ጠላት ማጥቃቱን አቁሞ አፈገፈገ። የወገን ጦር በመከላከያው ግንባር የተከመረውን የሶማሊያ ጦር እሬሳ ሲያይ ድል በማድረጉ ከፍተኛ ሞራል ተሰማው፤ በአመራሩ ላይ ከፍተኛ ዕምነት ጣለ። የመጀመሪያው ቀን ውጊያ ድል የክ/ጦሩ አርማ መለያ የሆነውን የአንበሳነት መንፈስ ጦሩ ተላበሰ። ከዚህ በኋላ የሶማሊያ ጦር ያደረጋቸው የማጥቃት ሙከራዎች ሁሉ በአመራሩም ሆነ በጦሩ ላይ ያሳደሩት ሥጋት አልነበረም። ክ/ጦሩ የተላበሰው የተዋጊነት መንፈስ በቆሬው መከላከል ውጊያ ብቻ ሳይሆን በሰሜኑም ጦር ሜዳ አሳይቷል።

በሶማሊያ በኩል መከላከያውን ጥሶ ያልፋል ብለው ያሰለፉት እግረኛ ጦር መሸነፉ ብቻም ሳይሆን የደረሰበት እልቂት በግንባሩ አመራር ላይ ከፍተኛ ድንጋጤን ፈጠረ። ከፊታችን የሚቆም ኃይል የለም የሚለው እብሪታቸው እንደጎማ ተነፈሰ። ከዚህ በኋላ ጧት በቁርስ፤ ቀን በምሳና ማታ በራት ጊዜ የማበሳጫ የመድፍ ተኩስ ቀጠለ፤ የሚያደርሰውም ጉዳት ቀላል አልነበረም። ይህን ሁኔታ በኛ መድፎች የርቀት አለመመጣጠን የተነሳ ማስቆም አልተቻለም ነበር፤ ሆኖም ጀግኖቹ የየመን መድፈኞች 122ሚ/ሜ መድፍና ቢኤም 21 ይዘው ቆሬ ሲደርሱ የሶማሊያውን የመድፍ ድብደባ በአጸፋ ተኩስ ለማስታገስ ችለዋል።

ዳለቻ ኮረብታ ከሐረር ጂጂጋ መንገድ በስተግራ የሚገኝና በ9ኛ እግረኛ ብርጌድ የመከላከያ ቀጠና ውስጥ ሲሆን ቆሬ ላይ ከተያዘው የመከላከያ ቦታ ገዢ መሬት ነው። የዳለቻ ኮረብታ በጠላት ከተያዘ የቆሬን መከላከያ ቦታን እርባና ያሳጣዋል። የሶማሊያ ጦር ጥቅምት 2 ቀን 1970 ዓ/ም ድንገተኛ ማጥቃት ሠንዝሮ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሎ ለአንድ ሌሊት ይዞት አድሮ ነበር ማግሥቱን ጧት የወገን ጦር በቦታው ላይ ያደረውን የሶማሊያ ጦር ከቦ በመደምሰስ ከረብታውን መልሶ ተቆጣጥሮታል። ጥቅምት 8 እና ጥቅምት 11 በኮረብታው ላይ ከፍተኛ ከሆነ የመድፍ ድብደባ በ10 ደቂቃ 80 የመድፍ አረር በማዝነብ ላይ እያለ አንድ የሶማሊያ አውሮፕላን ሊደበድብ መጥቶ ቦንብ ቢጥልም አልጎዳም፤ ሆኖም እሱ በአየር መቃወሚያ ተመቶ ወድቋል። ከዚህ በኋላ በእግረኛ ጦር ማጥቃት በመሰንዘር ኮሮብታውን ለመያዝ ያደረጋቸው ጥረቶች ሁሉ በወገን ጦር ብርቱ ተጋድሎ ሊሳኩ አልቻሉም ሆኖም በወገንም በጠላትም ላይ የደረሰው እልቂት ቀላል አልነበረም። የሶማሊያ ጦር  መሪዎች ከዚህ በኋላ የብረት አጥር የሆነውን የቆሬውን መከላከያ ይዞታ ሰብሮ ለማለፍ እንደማይችሉ ተገንዝበው በተለያዩ ሌላ አቅጣጫዎች ሙከራ ለማድረግ ወሰኑ። ይህም ኃይላቸው እንዲከፋፈልና እንዲዳከሙ አድርጓል።

አዲስ የነደፉት ዕቅድ የቆሬን ምሽግ በግራና በቀኝ አልፎ ከኋላ ባቢሌ ላይ መቁረጥ ነበር። በቀኝ በኩል በጉርሱም አድርጎ ባቢሌ መግባት ሲሆን በግራ በኩል ደግሞ ከፊቅ አቅጣጫ ባቢሌ መድረስ ሲሆን የሁለቱም ዕንቅስቃሴ በተመሳሳይ ጊዜ በተቀናጀ ሁኔታ እንዲመራ የታቀደ ነበር። በዚህም መሠረት በጉርሱም በኩል ወደ ባቢሌ ለማለፍ የተንቀሳቀሰው የሶማሊያ ጦር ጉርሱም ግንባር መከላከያ የያዘው 92ኛ ሕዝባዊ ሠራዊት ብርጌድና 023 አባት ጦር ሻለቃ አላሳልፍ ብሎ ገትሮ ያዘው እንዳውም የወገን ጦር ከምሽግ ወጥቶ 12 ኪ/ሜትር ያህል ጠላትን አሳዶ በመምታት በጠላት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ። ከዚያም በኋላ በጠላት የተሰነዘሩ ጥቃቶች በራሳቸው ላይ ዕልቂት ከማስከተል ውጪ ያስገኙት ፋይዳ አልነበረም።ስለዚህ ከጉርሱም ወደ ባቢሌ ለመንቀሳቀስ የታቀደው ዕውን ሊሆን አልቻለም።

ከቆሬ በግራ በኩል አልፎ ከፊቅ አቅጣጫ ባቢሌን ለመያዝ መንቀሳቀስ በጀመረ ጊዜ፤ ባቢሌን የመከላከል ግዳጅ የተሰጠው በኮ/ል ይርጋለም ተ/ሃይማኖት የሚመራው 5ኛ ሚሊሺያ ክ/ጦር (በኋላ 8ኛ ክ/ጦ የተባለው) ከባቢሌ ደቡብ 20 ኪ/ሜትር ርቀት አውሽሪፍ በተባለ ቦታ ሊገታው ችሏል። ጠላት በሁለቱም አቅጣጫዎች የወገንን መከላከያ ቦታዎች ሠብሮ ባቢሌ ለመግባት ያደረጋቸው ተከታታይ ሙከራዎች ውጤት አልባ ቢሆኑም ተስፋ ሳይቆርጥ በቀኝ ከጃርሶ በኮምቦልቻ ሐረር ምግባት፤ በግራ በኩል ደግሞ ከፈዲስ ሐረር መግባት የሚያስችል ዕቅድ ነድፎ ዕንቅስቃሴ ቀጠለ።

በመሃል አገር ለመልሶ ማጥቃት የሚደረገው ዝግጅት እስከሚጠናቀቅ ድረስ 3ኛ ክ/ጦር የብረት አጥር ሆኖ ቆይቶ በመልሶ ማጥቃቱ ምዕራፍ 5 ዕቅድ መሠረት ክ/ጦሩ በካራማራ መስመር ያለውን ጠላት እያጠቃ ጂጂጋ እንዲገባ ታዞ የካቲት 26 ቀን 1970 ዓ/ም ከቆሬ ምሽጉ ወጥቶ ወደ ካራማራ በር አመራ፤ በጉዞው ላይ የገጠመው ጠላት አልነበረም፤ ጂጂጋ ከተማም ክ/ጦሩ ከመድረሱ በፊት በብ/ጀኔራል ደሳለኝ አበበ የሚመራው 10ኛ ሚሊሽያ ክ/ጦር ተይዞ ስለነበር፤ 3ኛ ክ/ጦር በሰላም ደርሶ ከዚያም ወደ ደጋሃቡር አምርቶ የካቲት 29 ቀን ደጋሃቡር ገብቶ ጠቅላይ ሠፈሩን መሠረተ። ብዙም ሳይቆይ የምሥራቁን ድል በሰሜንም ለመድገም በመጋቢት ወር 1970 ከደጋሃቡር ተንቀሳቅሶ አዋሽ 40 ገብቶ የሚያስፈልገው የሰው ኃይልና ትጥቅ ተሟልቶለት አምበሳው 3ኛ ክ/ጦር ከነግርማ ሞገሱ ወደ ሰሜን ተንቀሳቀሰ። እኔ የክ/ጦሩ አካል ስላልነበርኩ አብሬ ስላልዘመትኩ ክ/ጦሩ በሰሜኑ ግንባር ስለሠራው ገድል የምለው የለኝም፤ ታሪኩን የተሟላ ለማድረግ በዚያ የነበራችሁ እባካችሁ ጀባ በሉን።

ብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው በአካዳሚክ ትምህርት አስተሳሰባቸው የዳበረ፤ በምዕራቡን ሆነ በምሥራቁ ወታደራዊ ሳይንስ ትምህርት የተካኑ፤ በተለያዩ ክፍሎችና በዓለም አቀፍ መድረክም ጭምር ልምድ ያካበቱ በመሆናቸው በግንባራቸው ከተሰለፈው የሶማሊያ ጦር አዛዥ ጋር ያደረጉትን የቼዝ ጫወታ (ውጊያ) በአሸናፊነት ለመወጣት አስችሏቸዋል።

የኢትዮጵያን ጦር ቆሬ ላይ ለድል ያበቁት የክ/ጦሩ ዕዝና ቁጥጥር ጥንካሬ፤ የጦሩ የውጊያ መንፈስ ጥንካሬና አልበገር ባይነት፤ የቆሬ መሬት ገጽ ከመንገዱ ውጪ ለሶማሊያ ሜካናይዝድ ጦር እንቅስቃሴ አለመመቸት፤ የሶማሊያ ጦር የሚለዋወጣቸው የሬድዮ መልዕክቶች እየተጠለፉ ዕቅዳቸው በቅድሚያ መታወቁ፤ ክ/ጦሩ የሚጠይቃቸው የሰውና የቁሳቁስ ድጋፍ አቅም በፈቀደ መጠን በቶሎ መድረሳቸው ለድሉ ድርሻ እንዳላቸው ቢታመንም ዋናው ግን የጀኔራል ይልማ ግዛው የሰከነ አመራር ነበር።እያንዳንዱ ክፍል ያለውን የማድረግ ችሎታ መዝኖ ተገቢውን ይዞታ በመስጠት፤ በግንባር የርስ-በርስ መረዳዳት በማረጋገጥ ኃይልን ከግንባር ግንባር በፍጥነት በማነቃነቅ፤ በትንሽ ኃይል ሠፊ ግንባር መሸፈንና ከአቅም በላይ የነበረን ጠላት ለስድስት ወር ያህል ገትሮ ማቆም ብቻ ሣይሆን ተስፋ አስቆርጦ የጥቃት አቅጣጫውን ማስቀየር የቻሉ አዛዥ ሆኑ።

ሥልጠና የሚፈጥረውን አቅም ከቀ.ኃ.ሥ. ሐረር ጦር አካዳሚ ተሞክሮ ስላላቸው በተገኘ ቀዳዳ ሁሉ የተወሰነውን የጦሩን ክፍል ወደ ኋላ እየሳቡ ሥልጠና እንዲሰጥ ያደርጉ ነበር። ለሥልጠናው ሥራ የ90ኛ ሚሊሽያ ብርጌድ አዛዥ የነበሩትና የኮርስ ጓደኛቸውን ብ/ጀኔራል ደሳለኝ አበበን ከብርጌድ አዛዥነት አንስተው ጊዜያው ኤታማዦር ሹም አድርገው የ10ኛ ክ/ጦር አዛዥ ሆነው ኮምቦልቻ ግንባር እስኪዞሩ ድረስ በሚገባ ተጠቅመውባቸዋል። የ74ኛ ሚ/ብርጌድ አዛዥ እንደነ ሌ/ኮሎኔል ይግዛው አብርሃ ያሉ ስፔሻል ፎርስ የሆኑ አዛዦም ለሥልጠናው ትልቅ ዕርዳታ አድርገዋል። የጦራቸውን የተዋጊነት አቅም እያሳደጉ ድልን አረጋግጠዋል።

ብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው የአላቸውን የወታደራዊ ሳይንስ ዕውቀትና በልምድ የዳበረ የተግባር ተሞክሮ በተግባር አውለው የቆሬን ድል አስገኝተዋል፤ ሆኖም በራሳቸው የሚተማመኑ በመሆናቸው የሚከተሉት አራት ነገሮች በሳቸው ዘንድ ፈጽሞ ተቀባይነት አልነበራቸውም።

1- ብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ በአግባቡ የሚፈጽሙ ግን ለበላይ የሚያጎበድዱና ልታይ ልታይ የሚሉ አልነበሩም። በተለይም ባለጊዜ የሆኑት የደርግ አባላት በሥራቸው ጣልቃ ሲገቡ ፈጽሞ የሚቀበሉ አልነበሩም፤ ይህም ጂጂጋ ላይ የደርግ አባላት በአዛዦች ሥራ ገብተው የተፈጠረውን የአመራር ምስቅልቅል ስለአዩ ነበር።

2- በበታቾቻቸው ዘንድ ርካሽ ተወዳጅነትን ለማግኘት የሚፈልጉ አልነበሩም። የሰጡት ትዕዛዝ ተፈጻሚነቱን በጥብቅ የሚከታተሉና የሚቆጣጠሩ፤ በማይፈጽም ላይ ጠንካራ እርምጃ የሚወስዱ ነበሩ።

3- በክፍሎች ውስጥ የሚመደቡ የሶቪዬት ወታደራዊ አማካሪዎች የተሻለ ወታደራዊ ዕውቀት የሌላቸው ግን ለመረጃነት የተመደቡ ናቸው ብለው የሚያምኑ በመሆኑ በቆሬ እስከነበሩ ድረስ ወታደራዊ አማካሪ አልተመደበላቸውም ነበር።

4- በወቅቱ ተፈጥሮ የነበረውን የሦስት ማዕዘን አመራር የማይቀበሉና ውጊያ በአንድ ሰው ዕዝ እንጂ በደቦ ሲመራ ለድል አያበቃም የሚል ጠንካራ ዕምነት ነበራቸው። ያለማወላወል ሠራዊቴን መምራት የምችለው ከፖለቲካ ነፃ ሆኜ ስሠራ ነው የሚል አቋም ስለነበራቸው የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል አልነበሩም።

ብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው ቆሬ ላይ ያስገኙት ድል ለጀኔራልነት ሹመት የሚያበቃቸው ነበር፤ ምናልባትም ከላይ የተጠቀሱት አቋማቸው ላለመሾማቸው ምክንያት ናቸው ተብለው በብዙዎች ዘንድ ይገመታሉ። በሰሜኑም ጦር ግንባር የሳቸው አመራር አምበሳው 3ኛ ክ/ጦርን ለከፍተኛ ድል አብቅቷል፤ ሆኖም አልተሾሙም፤ የጀግና ሜዳሊያም አልተሸለሙም። በወቅቱ የሜ/ጀኔራልና ከዚያም በላይ ማዕረግ ከነበራቸው የሠራዊቱ መሪዎች በአመራር ብቃት ይበልጡ እንደሆን እንጂ የሚያንሱ አልነበሩም። በግዳጅ ላይ ከሞቱ በኋላ መሾማቸው እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው የተባለው ተረት ብጤ ይመስላል። በሕይወት ሳሉ የጀኔራልነቱን ማዕረግ ለብሰው በሚወዱትና በሚወዳቸው አምበሳው ጦራቸው መሀል ቢገኙ ሁለቱንም ምንኛ ባስደሰተ ነበር፤ ግን አልሆነም። የአስር ዕልቅና ማዕረግ ለነበራቸው የደርግ አባላት የተሰጠ የጀኔራልነት ሹመት ለእሳቸው መነፈጉ፤ ያለፈ ታሪካችንን ላጤነ ለአገራቸው በጎ የሠሩ የተከፈላቸው ዉለታ ስለሌለ የቆሬው ብረት አጥር የብ/ጀኔራል ይልማ ግዛውም አለመሾም የሚደንቅ አይሆንም።

GC 656

መስከረም 2013